# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

አዲስ አበባ

ጥር 2007 ዓ.ም

ማውጫ

ክፍል አንድ .......................................................................... 1
መግቢያ .......................................................................... 1
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ .......................................................................... 1
የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር .......................................................................... 2
የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል .......................................................................... 3
የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ .......................................................................... 3
የኦዲቱ ዓላማ .......................................................................... 3
የኦዲት አካባቢ (Audit Area) .......................................................................... 4
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) .......................................................................... 4
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) .......................................................................... 4
የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን .......................................................................... 4
የኦዲቱ ዘዴ .......................................................................... 5
የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description) .......................................................................... 5
ክፍል ሁለት .......................................................................... 6
ግኝቶች .......................................................................... 6
የወጪ ንግድ ዘርፍ ዕቅድ ዝግጅት በተመለከተ .......................................................................... 6
የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና አፈጻጸምን በተመለከተ .......................................................................... 7
የእቅድ አፈጻጸም መረጃ ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ .......................................................................... 8
የወጪ ምርት አፈጻጸም የክትትል እና ግምገማ አሰራርን በተመለከተ .......................................................................... 10
መረጃዎች መሰብሳብ፤ማዳራጀት፤መተንተን እና ማስራጪትን በተመለከተ .......................................................................... 11
በኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች የመሠረተ ልማት አውታሮች መሟላቱን በተመለከተ .......................................................................... 12
በኢንደስትሪ ዘርፍ ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራትን በተመለከተ .......................................................................... 14

ለኢንዱስትሪዎች የሚሰጥ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ አሰራርን በተመለከተ .........15
በወጪ ምርት ለተሰማሩ ፋብሪካዎች የጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ጥራትን በተመለከተ..........18
ለፋብሪካዎች የግብዓት አቅርቦት ትስስርን በተመለከተ ......................................20
ለወጪ ምርት ለማሳደግ የጥናትና ምርምር ሥርፀት ሥራዎችን በተመለከተ ..............20
ለወጪ ንግድ ማምረት የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግን በተመለከተ.......................22
ለወጪ ምርቶች የገበያ መረጃ እና ድጋፍን በተመለከተ ......................................23
**መደምደሚያ** ..........................................................................25
**ክፍል አራት** ..........................................................................28
**የማሻሻያ ሃሳቦች**.......................................................................28
አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች...........................................................31
አባሪ 2፡ ለዝርዝር ኦዲቱ በናሙና የተመረጡ......................................................33
አባሪ 3፡ የአሰራር ሥርዓት ትንተና (Process description) ................................34
አባሪ 4፡ ድርጅታዊ መዋቅር...................................................................35

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. ኢትዮጵያ ሀገራችን የግብርና እና የኢንዱስትሪ ዘርፉ መመጋገብ እንዲኖር በማድረግ በመቀጠል ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር እንድትሸጋገር የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ በዚሁ መሰረት የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች የኤክስፖርት መር አቅጣጫን በመከተል ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ (የውጭ ምንዛሪ) ለማሳደግ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባለሀብቶች በተቀናጀ መልኩ ወደ ልማት እንዲገቡ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ባለፉት አመታት ለተመዘገበው ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ወሳኝና የመሪነት ሚና የነበረው የግብርናው ዘርፍ ክፍለ ኢኮኖሚ እንደሆነ የሚታወቅ ቢሆንም የኢንዱስትሪው ዘርፍም በየጊዜው እየተሻሻለ ለተመዘገበው የኢኮኖሚ እድገትና ልማት የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡
2. ምንም እንኳን የኢንዱስትሪ ዘርፍ ሲባል ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያለውን እንደ ኮንስትራክሽን፣ የኃይል ምንጭና የማዕድን ዘርፎችን የሚያካትት ቢሆንም በዚህ ዕቅድ የተሸፈኑት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ በተለይም የከፍተኛና መካከለኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ እንዲሁም የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡
3. አገራችን የኢንዱስትሪ ዘርፍ በጥቅሉ ከ1997-2001 ባሉት አመታት በየአመቱ በአማካይ የ9.9 በመቶ እድገት አስመዝግቧል፡፡ ዘርፉ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በአማካይ ወደ 12 በመቶ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የማኑፋክቸሪግ ንዑስ ዘርፍ /አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችና መካከለኛና ከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች/ ተጠቃለው ያላቸው ድርሻ በአማካይ ወደ 5.5 በመቶ አካባቢ ነው፡፡ ለወጪ ንግድ የሚውለው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ውጤትም ከጠቅላላ የወጪ ንግድ ያለው ድርሻ በአማካይ ወደ 10 በመቶ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ሁኔታዎች ዘርፉ አሁንም በጠባብ መሰረት ላይ ያለና በቀጣይ በስፋት ሊሰራበት የሚገባ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

### የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ

4. "ፈጣንና ቀጣይነት ባለው ዕድገት ላይ የተመሰረተ፣ ተወዳዳሪ የሆነና በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚናን የሚጫወት የኢንደስትሪ ዘርፍ በ 2015 ዓ.ም እውን ማድረግ" ነው፡፡

#### የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ

5. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ አካባቢ በመፍጠር፣

ለልማታዊ ባለሀብቱ የላቀ አገልግሎትና ድጋፍ በመስጠት እና የዘርፉን የሰው ሀብትና የቴክኖሎጂ አቅም በማሳደግ የኢንደስትሪውን ዘላቂ ዕድገት ማረጋገጥ ነው፡፡

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ እሴቶች**

6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከተሉት እሴቶች አሉት፡፡ ለልማታዊ ባለሀብቱ ስኬት መትጋት፣ ምንግዜም ለመማርና ለመለወጥ ዝግጁ መሆን፣ ለፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግርና ተጠቃሚነት መስራት፣ ለአካባቢ ደህንነትና እንክብካቤ መቆም፣ የሠመረ ቅንጅታዊ አሰራርን መተግበር እና ፍትሀዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማራመድ ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር

**ዓላማ**

7. "መ/ቤቱ ከቀድሞው የተሸለ ተግባርና ሃላፊነት ኖሮት ዘርፉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እንዲችል፣ በየጊዜው እያደገ የመጣውን አጠቃላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥና ኢንዱስትሪው በአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫወት፣ አገራችንም ከድህነትና ኋላቀርነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ እንዲኖራትና በኢንዱስትሪ እንድትበለጽግ ማድረግ፡፡"
የሚል ነው፡፡

**ሥልጣንና ተግባር**

8. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች አሉት፡-

- ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
- የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤
- ስትራቴጂያዊ ትኩረት ለሚሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ ይሰጣል፤
- ለአገር ውስጥና ለውጭ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤
- ለኢንቨስተሮች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል ሁሉም አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል የሚሰጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲመሩና በሕግ አግባብ ወደ ግል ይዞታ እንዲዛወሩ መደረጋቸውን ያረጋግጣል እና
- የኢንዱስትሪ፣ የዘርፍና የሙ--ያ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ማድረግ ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

9. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መ/ቤት አንድ ሚኒስትር እና ሶስት (3) ሚኒስትር ዴኤታ የሚመራ ሲሆን በቀጥታ ለሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ ዘጠኝ ዳይሬክቶሬቶች አሉት፡፡ በአጠቃላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ 16 ዳይሬክቶሬቶች፣ ለተለያዩ የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ድጋፍ የሚሰጡ 7 ኢንስቲትዩቶች፣ እና 2 ኮርፖሬሽኖች እና 2 ኤጀንሲዎች አሉ፡፡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር ስዕላዊ መግለጫ **በአባሪ 4** ተያይዟል፡

### የሰው ኃይል

10. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት እንዲያስችለው እስከ ታህሳስ 2007 172 የሰው ሀይል ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ 99 ሴቶች እና 73 ወንዶች ሲሆኑ 64 ከዲፕሎማ በታች ፣ 34 ዲፕሎማ ፣ 66 ዲግሪ እና 8 ማስተርስ ያላቸው መሆኑን በታህሳስ/2007 ዓ.ም ከቀረበው ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

### የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

11. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መ/ቤት የፋይናንስ ምንጭ በዋነኝነት ከመንግስት የሚመደብ በጀት ሲሆን በተጨማሪም ለኢንዱስትሪ ዞን ግንባታ ከአለም ባንክ በሚሰጥ ብድር እና ለተለያዩ ልማቶች የሚውል ከገንዘብ ሚኒስቴር የሚፈቀድ የመንግስት የትርፍ ገንዘብ ድርሻ ፈንድ እንዲሁም ዘርፉን ለመደገፍ የተለያዩ ፕሮጀክቶች በዩናይትድ ኔሽን እና በሌሎችም አጋሮች እንደሚደገፍ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

### የሚኒስትር መ/ቤቱ የበጀት አጠቃቀም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| | የተመደበ በጀት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መደበኛ በጀት | ካፒታል በጀት | ጠቅላላ በጀት | ስራ ላይ የዋለ | ልዩነት |
| 2004 | 20,598,136.46 | 217,000.00 | 20,815,136.46 | 19,909,426.98 | 905,709.48 |
| 2005 | 22,545,646.06 | 63,191,320.00 | 85,736,966.06 | 30,220,592.69 | 55,516,373.37 |
| 2006 | 25,890,087.75 | 74,549,000.00 | 100,439,087.75 | 67,323,360.33 | 33,115,727.42 |

### የኦዲቱ ዓላማ

12. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢንዱስትሪ ምርቶች ኤክስፖርት (የወጪ ንግድ) አፈጻጸም በቁጠባ፤ በብቃት እና በስኬታማነት ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፤ በዚህ ዙሪያ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ወይም የአሰራር ግድፈቶችን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

13. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "የኢንዱስትሪ ምርቶች ኤክስፖርት (የወጪ ንግድ) አፈጻጸም ሥራ ኢኮኖሚ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም የሚል ነው"፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue)

14. ከላይ በተገለጸው የኢዲት አካባቢ ሥር አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ተመርጠዋል፡፡ እነሱም፡-
    1. ሚ/ር መ/ቤቱ የጥናትና ምርምር ተግባሮችን ማከናወንና የአቅም ግንባታ ስራዎችን አቀናጅቶና አሟልቶ መተግበሩን መገምገም፤
    2. በወጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ኢንደስትሪዎች የግብአት አቅርቦትና ምርት ትስስር ስራዎችን ማጠናከር፣ቁልፍ ሚና ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ለመስራት ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን እንዲሁም ተፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለሚመለከታቸው የሚሰራጭበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ

ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

15. ከላይ የተመረጡት አራት የኦዲት ጭብጦች (Audit Issues) ለመመዘን የሚያስችሉ 25 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑ የሚኒስቴሩ መቋቋሚያ አዋጅ፣ የኢንስቲትዩቶቹ መቋቋሚያ ደንብ፤ስትራቴጂክ ዕቅዶች፣ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ የሥራ መመሪያ እና መልካም ተሞክሮዎች፣ የሥራ አመራር ቃለ ጉባኤዎች እና የቤሔራዊ የኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤዎችን ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ሥራው የሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን

16. ኦዲቱ የተከናወነው መ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት እና በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) የተከናወነ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ ከ2004 እስከ 2006 በጀት ዓመት

ድረስ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የወጭ ንግድ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወኑ ስራዎችን እና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ ያሉ ጉልህ ጉዳዮች አካቷል፡፡

17. የተከናወነውም በዋናነት በኢንዱስትሪ ሚኒስትር መስሪያ ቤት እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር ባሉ ኢንስቲትዩቶች፣ በናሙና በተመረጡ ፋብሪካዎች የዘርፍ ማህበራት ነው፡፡ እነሱም 13 ፋብሪካዎች፣ እነርሱም 3 ከጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች፣ 3 ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች፣ 3 ከኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓት ኢንደስትሪዎች፣ 1 ከስጋና ወተት ኢንዱስትሪ እና 3 ከብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች ፣ 2 የዘርፍ ማህበራት 1 ኢንስቲትዩት በናሙና ተመርጠው በኦዲት ተካተው ታይተዋል፡፡ በናሙና ተመርጠው በኦዲት የታዩ ፋብሪካዎች እና ማህበራት ዝርዝር **በአባሪ 2** ተመልክቷል፡፡

## የኦዲቱ ዘዴ

18. በኦዲቱ ወቅት ከኦዲቱ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች በመከለስ፣ በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አራት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሥራ ኃላፊዎች፣ ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንስቲትዩት፣ ለ2 የዘርፍ ማህበራት እንዲሁም ለ 13 ኢንዱስትሪዎች በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው ሃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ መረጃዎች በመሰብሰብ እና በመከለስ በመተንተን ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 8 የሰርቬይ መጠይቅ (በፋክስ) እና 2 በኢሜል በመላክ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description)

20. መንግስት ያስቀመጠውን GTP ዕቅድ በአለም አቀፍ ተወዳዳሪ የኢንዱስትሪ ምርት ማምረት፤ ለኢንዱስትሪ ዘርፍ መሪ፣ ስትራቴጂክና አመታዊ እቅድ ማዘጋጀት፣ መረጃዎች መሰብሳብ፣ ማዳራጀት፣ መተንተን እና ማሰራጨት፤ መሠረተ ልማትን እንዲሞላ ማድረግ፤በዘርፉ ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት፣ ከባለድረሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር፤ የግብዓትና ምርት ትስስርና ቅብብሎሽ አሰራር ማዘርጋት፣ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ማከናወን፤ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መድረግ፤ የገበያ መረጃ እና ድጋፍ መስጠት፣ በአለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ኢንዱስትሪ ምርት ማምረትና መሸጥ ነው፡፡ ስዕላዊ መግለጫ (Process Description) **በአባሪ 3** ይመልከቱ፡፡

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## የወጪ ንግድ ዘርፍ ዕቅድ ዝግጅት በተመለከተ

21. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በየኢንዱስትሪ ዘርፎቹ የወጪ ንግድ ገቢ በስትራተጂክ ዕቅዱ መጨረሻ ያስቀመጣቸውን ግቦች ማሳካት ይገባል፡፡ የስትራስቴክ ዕቅዱንም በሚያዘጋጅበት ወቅትም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ሊያሳትፍ በቅንጅት የሚሰሩበትን ሁኔታ ሁሉ ሊያመቻች ይገባል፡፡
22. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኤክስፖርት ዕቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም ዕቅዱን ሲያዘጋጅ ከባለሃብቶቹ እና መንግሥታዊ የሆኑ ወሳኝ ባለድርሻ አካላትን (የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን፤የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ንግድ ሚኒስቴር፤የግብርና ሚኒስቴር እና ሌሎች ተቋማት) ጋር፣ በበቂ ሁኔታ በመመካከር እና በመቀናጀት ስለማዘጋጀቱ መረጃው ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡ ዕቅዱንም ሲያዘጋጅ በተጨማሪም በዘርፉ ከተሠማሩ ባለሃብቶች ጋር የኤክስፖርት እቅድ ዝግጅት ወቅት በቅንጅት ከጥሬ ዕቃ አቅርቦት ጀምሮ እስከ ምርት ማምረት እና ለአለም ገበያ መሸጥ ድረስ ያለውን የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት ለችግሮቹ የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ ተግባራዊ ስለመደረጉ መረጃው ኦዲቱ እሰከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡
23. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የዘርፉ ፋብሪካዎች መካከል በወጪ ንግድ ምርት ለተሠማሩ ፋብሪካዎች በወቅቱና በሚፈለገው መጠን ድጋፍ እንደማያገኙ ገልጸዋል፡፡
24. የኤክስፖርት የመነሻ ዕቅድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ከተጠሪ ኢንስትቲዩቶች ጋር ቢዘጋጅም፣ የመጨረሻው ዕቅድ የሚዘጋጀው በዘርፉ ከተሰማሩ ባለሃብቶች/ኩባንያዎች ጋር በመወያየት ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ ነው የሚል መልስ
25. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኤክስፖርት ዕቅድ በአገር አቀፍ ደረጃ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚመሩት ብሔራዊ ኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ የሚዘጋጅ ሲሆን በሥሩ የግባዕት፣ የከስተምና ሎጀስቲክ እንዲሁም ፋይናንስና ቴክኖሎጂን የሚመለከቱ ሦስት ንዑሳን ኮሚቴ ተዋቅረው ዕቅድ እንደሚዘጋጅ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡ የግብዓት ዕጥረትን በተመለከተም በገበያው ሥርዓት ይፈታል ተብሎ ስለሚታመን ጣልቃ አለመግባታቸውን ነገር ግን ገበያው ሊፈታ ያልቻለውን ብቻ በመለየት ጣልቃ መግባት እንደጀመሩ ገልጸዋል፡፡ በስራቴጂካዊ የወጪ ምርቶች ላይ

ያለውን የግባዕት ችግር ለመፍታት ኢንድስትሪ ምርቶች ግብዓት አቅርቦት ድርጅት መቋቋሙንም በተጨማሪ ገልጸዋል፡፡ በዕቅድ ዝግጅት ወቅት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ እና በተናጠል በሚሰሩ ሥራዎች ላይ በመመካከር እና መግባባት ከተደረሰ በኋላ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራሮች የሚመሩባቸው እና አባላት የሆኑባቸው ንዑሳን ኮሚቴዎች ዝርዝር ዕቅድ እንደሚዘጋጅ ነገር ግን አንዳንዶቹ ኮሚቴዎች በተቀመጠው የግምገማ ወቅት ጠብቀው ግምገማ የማያካሄድ (የማያካሂዱ) መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

26. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ክፍሉ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጅ የኤክስፖርት ዕቅድ ከባለድርሻ አካላት እና በንዑሳን ኮሚቴዎች ጋር በመመካከር እና በመቀናጀት ስለመዘጋጀቱ ማስረጃው ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

27. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኤክስፖርት እቅድ ዝግጅትና ተግባራዊ ለማድረግ የሚከሰቱ ችግሮችን በዝርዝር በማስቀመጥ አስቀድሞ ለመከላከልና ከተከሰተም በኋላ አፋጣኝ መፍትሄ ካልተሰጠው በዘርፉ የተቀመጠውን እቅድ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ የፈጠረ መሆኑ እና የታለመውን ግብ እንዳይመታ እንቅፋት ይሆኗል፡፡

## የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና አፈጻጸምን በተመለከተ

28. የተዘጋጀው የኤክስፖርት ዕቅድ በታሰበው መሰረት እየተከናወነ መሆኑ አፈጻጸመ ላይ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ በአፈጻጸም ላይ የታዩ ችግሮችና ክፍተቶችም ካሉ በአፋጣኝ መፍትሔ በመፈለግ ዕቅዱ እንዲሳካ ሊደረግ ይገባል፡፡

29. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንዲሁም በኢንዱስትሪ ዘርፍ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (ከ2003-2007 ዓ.ም) መሠረት ከ2003 እስከ 2006 ዓ.ም. ባለው አራት የዕቅድ አመታት የዕቅድ አፈጻጸም ሲታይ

- ከቆዳና የቆዳ ውጤቶች የሚገኘው 1,255.4 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በእቅድ የተቀመጠ ሲሆን ክንውን 473.05 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (38%) መሆኑ፣
- ከጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ በእቅድ የተያዘው 1,450 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ክንውኑ 356.21 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (24.63%) መሆኑ፣፤
- ከአግሮ ፕሮሰሲንግ ምርቶችን በእቅድ የተያዘው 573 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ክንውን 202 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (35.24%) መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድና እቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. ይህንን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃለፊዎች በሰጡት መልስ መሠረት በጣም ዝቅተኛ አፈጻጸም የተመዘገበበት ምክንያቶች መካከል የግብዓት አቅርቦት በሚፈለገው

ጥራትና ብዛት መጠን አለመገኘት፣ኩባንያዎቹ ወደ አገር ውስጥ ገበያ ማዘንበል፣ የፋብሪካዎቹ ምርት ትስስር (Integration) በሚፈለገው ፍጥነት አለማካሄድ፣የኩባንያዎች የማኔጅመንትና ቴክኒክ አቅም ውስንነት፣ በኢንቨስትመንት ሂደት ያሉ ፕሮጀክቶች መዘግየት እና በመንግሥታዊ አገልግሎቶች /ድጋፍ ሰጭ ላይ የነበሩ ውስንነቶች እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡

31. ሚኒስቴሩ መ/ቤቱ ሊያከናወን ያቀዳቸው የውጪ ንግድ ምርት በዕቅድ ዝግጅቱ ወቅት በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትና በመመካከር ያልተዘጋጀ በመሆኑ ዕቅድ አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ የኢንደስትሪ እድገት በታቀደለት መሰረት እንዳይሆን የበኩሉን አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

## የእቅድ አፈጻጸም መረጃ ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ

32. የኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ አፈጻጸም መረጃዎች በትክክል ሊመዘገቡና ትክክለኛ መረጃ እየተላለፈ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ መረጃዎቹም ተጠናቅረው ሊያዙና ለሚመለከታቸቸው አካላት በሚፈለግበት ወቅት ሊቀርብ ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በ2005 ዓ.ም የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት የወጪ ንግድ አፈጻጸም 98,988,000 እና በ2006 ዓ.ም 111,350,000 አሜሪካን ዶላር ተብሎ የተያዘ ሲሆን በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በ2005 ዓ.ም በቀረበው ሪፖርት ላይ ግን 97,521,115 እና በ2006 ዓ.ም 111,074,645 አሜሪካ ዶላር በመሆኑ (በ2005 የአሜሪካን ዶላር 1,466,885 እና በ2006 የአሜሪካን ዶላር 275,355 ልዩነት መኖሩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተያዘው በመብለጥ የሚያሳይ መሆኑ) እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት መሠረት የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ በ2005 ዓ.ም 123,440,000 አሜሪካ ዶላር እና በ2006 ዓ.ም 132,950,000 አሜሪካ ዶላር ሲሆን በገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል የቀረበ ግን በ2005 ዓ.ም 121,073,599 እና በ2006 ዓ.ም 130,267,531 አሜሪካን ዶላር መሆኑን፣ (በ2005 የአሜሪካን ዶላር 2,366,401 እና በ2006 የአሜሪካን ዶላር 2,682,469 ልዩነት መኖሩን ) በኦዲት ወቅት ከተከለሰው የሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከ2005-2006 ዓ.ም እና ከጉምሩክ የሚቀረብ የአስኩዳ ሲስተም ከ2005-2006 ዓ.ም መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ 1

| የውጭ ንግድ ገቢ በአሜሪካን ዶላር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ንዑስ ዘርፍ | | በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ልዩነት የሚ/ር መ/ቤቱ |
| የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት | 2005 | 98,988,000 | 97,521,115 | 1,466,885 |
| | 2006 | 111,350,000 | 111,074,645 | 275,355 |
| የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ | 2005 | 123,440,000 | 121,073,599 | 2,366,401 |
| | 2006 | 132,950,000 | 130,267,531 | 2,682,469 |

34. ይህንን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ አልሚ ምግብ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በውጭ ምንዛሪ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች /ለአለም ምግብ ድርጅት በአገር ውስጥ ገበያ ስለሚሸጡ እና ይህንን መረጃ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ስለማያውቀውና እንዲሁም ባለስልጣኑ ሌሎች (Others all Ministerial Office) ብሎ የሚያስቀምጣቸው ኤክስፖርት የተደረጉ በጣም በርካታ ምርቶች በአንድ ላይ አሰባስቦ ሪፖርት እንደሚልክላቸውና ይህንንም የዕቃዎች መለያ ቁጥር (በHS code) መሠረት በማድረግ የሚለዩ መሆኑና በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የኦቶ ኬስለር የጓንት ምርት ፋብሪካ ከጎንደር ኤክስፖርት ያደረገውን ምርት በባለሥልጣኑ ባለመመዝገቡ ምክንያት የተፈጠረ ልዩነት ነው ቢሉም ለተጠቀሰው ማስረጃ ባለመቅረቡ እና ለሌሎቹ ምላሽ ስላልተሰጠ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

35. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርብ የኤክስፖርት አፈጻጸም ሪፖርት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከሚቀርበው ብልጫ ያለው በመሆኑ ሪፖርት አፈጻጸሙና አገሪቷ ከንዑስ ዘርፎቹ ያገኘችው የውጭ ምንዛሪ ትክክለኛ መረጃ የትኛው እንደሆነ ማረጋገጥ አያስችልም፡፡

36. በናሙና ተመርጠው በኦዲት ከታዩት ፋብሪካዎች መካከል በአሸራፍ ቁራ ኃ.የተ.የግል.ማህበር ወደ ውጪ የሸጠው የሥጋ ምርት በ2004 ዓ.ም አጠቃለይ ከውጪ ንግድ የተገኘ 187,507.79 አሜሪካ ዶላር ሲሆን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት የቀረበው ግን 370,000 የአሜሪካን ዶላር መሆኑና፤

37. እንዲሁም በኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር የ2006 በጀት ዓመት የኤክስፖርት ሽያጭ አፈጻጸም ሪፖርት መሠረት ዕቅድ 11,283,000፤ክንውን 7,262,000 የአሜሪካ ዶላር ሲሆን፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ግን ያቀረበው የኤክስፖርት ሽያጭ አፈጻጸም ሪፖርት መሠረት ዕቅድ 15,081,000፤ክንውን 7,440,000 የአሜሪካ ዶላር መሆኑን ከተከለሱ

የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና ከፋብሪካዎቹ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

38. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ክፍሉ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አንዳንድ ጊዜ የመረጃ ክፈተት ሊኖር እንደሚችልና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርብልተ የግምት ዋጋ ስለሆነ ከገቢዎችና ጉምሩክ የተገኘው መረጃ ትክክለኛ እንደሆነ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

39. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በውጪ ንግድ ሪፖርት አቀራረብ ዙሪያ ከኩባንያዎቹ (ከፋብሪካዎቹ) እና ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚቀርብ የወጪ ንግድ አፈጻጸም በትክክል በማመሳከርና ልዩነት ሲኖር ከድርጅቶቹ ጋር በመነጋገር ልዩነቱን በማስታረቅ ተመሳሳይ ሪፖርት አለማቅረቡ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ ለሚመለከታቸው አከላት ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ እንዲያቀርብ ያደርገዋል፡፡

## የወጪ ምርት አፈጻጸም የክትትል እና ግምገማ አሰራርን በተመለከተ

40. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትልና የግምገማ አሰራር የዘርፉን እቅድ አፈጻጸም በሚመለከት ወሰኝ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር ሊያደርግ ይገባል፡፡ በሚደረጉትም ስብሰባዎችና ውይይቶች የሚገኙ መረጃዎችን በመተንተን ለኢንስቲትዩቶችና ለፋብሪካዎች የግምገማ ሪፖርትና ግብረ መልስ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

41. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትልና የግምገማ አሰራር የዘርፉን እቅድ አፈጻጸም በሚመለከት ወሰኝ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረጉ ስብሰባዎች፤ውይይቶችና ከውይይቶቹ የሚገኙ መረጃዎችን በመተንተን ለኢንስቲትዩቶችና ለፋብሪካዎች የግምገማ ሪፖርት /ግብረ መልስ የማይልክና ክትትል የማይደረግ መሆኑን በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ከአይካ ቴክስታል፤ ባህዳር ጨርቃጨርቅ፤ ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ፤ኮምቦልቻ ታኔሪ፤አንበሳ ጫማ ፋብሪካ፤ኒው ዊንግ ጫማ ፋብሪካ፤ቴክኖ ሞበይል ፋብሪካ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፤

42. ጉዳዩን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በየዘርፍ ደረጃ በየሳምንቱ እና በየወሩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራሮች የሚመሩት ግምገማ በማካሄድ ለኢንስቲትዮች እና ወሳኝ ለሆኑ ባለድርሻ አካላት በቀጥታ ግብረ መልስ ይሰጣቸዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ፋብሪካ ግብረ መልስ የመላክ አስፈላጊነት በሌሎች ልምዱ ካለ ይሰጠን እና ጠቀሜታው በቀጣይ የሚታይ ይሆናል፡፡ የኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በአፈፃፀም ላይ በየወቅቱ የሚሰጣቸው ግብረ መልሶች ለሚመለከታቸው አካላት የሚላክ መሆኑን ገልጿል፡፡

43. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ግብረ መልሱ ስለመለኩ ማስረጃ

ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃው አልቀረበም፡፡ መስጠት አልተቻለም፤

44. በኢንስቲትዩቶች በኩል የክትትልና የግምገማ ሥራ በመስራት የተዘጋጀውን ግብረ መልስ በመላክ በሚመለከታቸው የዘርፍ ማህበራት በኩል እንዲደርሳቸው እና ተግባራዊ መደረጉና አለመታወቁ ከዘርፉ የሚጠበቀውን የውጭ ምንዛሪ ላለመገኘቱ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

## መረጃዎች መሰብሳብ፤ማዳራጀት፤መተንተን እና ማስራጨትን በተመለከተ

45. የኢንዱስትሪ ሚኒስትር በማዕከል የተደራጁ መረጃዎችን የመረጃ ኔት ዎርክ በመዘርጋት ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ተጠቃሚዎች በተለያዩና በተሻሻሉ የስርጭት ዘዴዎች ተደራሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በማእከል የሚደራጁት ወቅታዊ፣ አለም አቀፍ እና የተሟሉ ዋና ዋና መረጃዎች በየጊዜው የማሰባሰብ፣ የማጠናከር፣ የማደራጀትና የመተንተን ስራዎችን መስራት ይገባል፡፡

46. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ወቅታዊ፣ትክክለኛና የተሟላ መረጃ በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና ለሚመለከታቸው የዘርፉ ተጠቀሚዎች በተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በአንድ ማዕከል የመረጃ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግተው ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተደረገው የፋብሪካ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

47. በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጅያዊ ውጤት ተኮር እቅድ (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት የኢንዱስትሪው የማምረት አቅምን ለማሳደግ የሚያግዝ የመረጃ ሥራ አመራር ሥርዓትን ለማሻሻል ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም አግባብ የሆኑ መረጃዎችን (ምርጥ ተሞክሮዎች፣ የደረጃ፣ የምርምርና ስርፀት ውጤቶች፣ አዳዲስ የለውጥ መሳርያዎች እና የመሳሰሉት) በየጊዜው የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና የማጠናቀር ለማከናወን ዕቅድ ቢይዝም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በማዕከል የሚደራጁት ወቅታዊ፣ አለም አቀፍ እና የተሟሉ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎች (ምርጥ ተሞክሮዎች፣ የምርምርና ስርፀት ውጤቶች፣ አዳዲስ የለውጥ መሳሪያዎች፤የግብይት እና የመሳሰሉት) መረጃዎች በየጊዜው የማሰባሰብ፣ የማጠናከር፣ የማደራጀትና የመተንተን ሥራ እየተሰራ የማይደርሳቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከአይካ ቴክስታይል፤ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ፤ባህርዳር ጨርቃጨርቅ፤ኮመቦልቻ ታኔሪእና ቴክኖ ሞባል ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

48. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ጉዳዩን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የብሔራዊ ኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ የሚሰጠው ግብረ መልስ (ቃለ ጉባኤ) በኢሜይል ለኢንስቲትዩቶች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች የሚላክ እና ስለ አፈፃፀሙም ክትትል የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለባለሀብቶች የሚፈልጉትን መረጃ በአንድ ማዕከል እንዲያገኙ እስከአለፈው ሰኔ ድረስ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የነበረው የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ያከናውን እንደነበረ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

49. ከዚህ በተጨማሪም የመረጃ አሰጣጥ አገልግሎት እስካሁን በእቅድና መረጃ ዳይሬክቶሬት በኩል እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ነገር ግን በተደራጀ መልኩ እንዲሆን ተብሎ በውጭ ባለሙያዎች ጥናት ተደርጎበት በሥርዓት ዝርጋት ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

50. ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም አግባብ የሆኑ መረጃዎችን (ምርጥ ተሞክሮዎች፣ የምርምርና ስርፀት ውጤቶች፣ አዳዲስ የለውጥ መሳሪያዎች፣የግብይት እና የመሳሰሉት) በየጊዜው ለሚመለከተው አካላት ተደራሽና ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች እንዲደርሳቸው የሚያገኙበት ስርዓት ካልተመቻቸ ባለሀብቶቹን ለተጨማሪ የጊዜና የገንዘብ ወጪ ሊዳርጋቸው ይችላል፡፡

## በኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች የመሠረተ ልማት አውታሮች መሟላቱን በተመለከተ

51. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት በሚያከናውኗቸው ድጋፎችና አገልግሎቶች ሂደት ከክልሎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

52. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጅያዊ ውጤት ተኮር እቅድ (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ለማድረግ ለኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ-ልማት አውታሮች እንዲስፋፉ ለማድረግ ዕቅድ ይዞ ነበር፡፡

53. ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት

- ባህርዳር ጨርቃጨርቅ አ.ማ. በፊት ከነበረው የፋብሪካ የኃይል ፍላጎት 4 ሜጋዋት ሲሆን አዲስ ማሽን ሲተከል አጠቃለይ 10.5 ሜጋዋት በማስፈለጉ ለኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን በተደጋጋሚ በግቢያቸው ውስጥ ካለው ንዑስ ጣቢያ

ኃይል እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም ከሌላ ንዑስ ጣቢያ ወደ 6 ኪ.ሜ. ላይ የሚገኝ በ6 ሚሊዮን ብር ከፍለው እንዲያስገቡ በመደረጉ ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉን ከፋብሪካው ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፤

- በደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ፋብሪካ የዳሽን ሲሚንቶ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ተጨማሪ 300 ቶን በቀን የሚያመርት ፋብሪካ ግንቦት 2002 ዓ.ም. የተጠናቀቀ ሲሆን እስከ እስከ ጥቅምት/2007 ዓ.ም ድረስ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ባለማግኘቱ ምክንያት ምርት እያመረተ እንዳልሆነ ከፋብሪካው ሥራ አስፈጻሚ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፤
- በባህርዳር ጨርቃጨርቅ አ.ማ.፤በደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካ፤ በቴክኖ ሞባይል መጋጣጠሚያ ፋብሪካ፤በኒው ዊንግ ቆዳ ፋብሪካ፣ በቤዛ ኢንዱስትሪ እና በአይካ አዲስ ቴክስታይል ፋብሪካ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና መዋዥቅ ምክንያት ማሽኖቻቻውን እንዲበላሹ እና ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸው እንዲሁም በምርትና ምርታማነት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ መሆኑን

በመስክ ጉብኝት ወቅት ከፋብሪካው ኃላፊዎች ከተደረገው ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል።

54. ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባህርዳር ጨርቃጨርቅን በተመለከተ በቂ ድጋፍ የተደረገለት መሆኑና በተለያየ ጊዜ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ተጠይቀው ግቢ ውስጥ ያለው ሳብስቴሽን ፋብሪካው የሚፈለገውን ያህል ኃይል ማቅረብ ስለማይችል ከግቢ ውጭ ከሌላ ሳብስቴሽን የኤሌክትሪክ ኃይል ለማስገበት በረዥም ጊዜ ክፍያ እንዲስተናገድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረ ቢሆንም ፋብሪካው ከግቢው ውስጥ ካልተሰጠኝ በማለት ፍቃደኛ ባለመሆኑ የተፈጠረ ችግር መሆኑን፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በረጅም ክፍያ የማይቻል መሆኑን በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት የተገለጸ በመሆኑ መሆኑን ገልጸዋል። በደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ፋብሪካ ለሚያካሂደው የዳሽን ሲሚንቶ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ተጨማሪ 300 ቶን በቀን የሚያመርት ፋብሪካ የተጠናቀቀው በ2002 ሳይሆን በ2005 ዓ.ም. መሆኑ ነው ቢሉም የደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ዋና ስራ አስፈጻሚ በ2002 ዓ.ም የተጠናቀቀ መሆኑን ገልጸዋል።
55. የኃይል አቅርቦት ችግርን አስመልክቶ ከውሃና ኢነርጂ ሚንስቴር እና ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ጋር ውይይት መደረጉን እና በውይይቱም ችግሮቹ እንዳሉ ታምኖ፤በደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካ፣ በአይካ አዲስ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና መዋዥቅ

ችግር የተፈታ መሆኑ፤እንዲሁም በሌሎች ኢንዱስትሪዎች የኃይል እጥረትን ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት እንደሚደረግ እና ኃይል ከመቋረጡ በፊት ከመገናኛ ብዙኃን በተጨማሪ ሌሎች የማሳወቂያ መንገዶችን / በስልክ፣ ኢ-ሜል፣ ወዘተ/ በመጠቀም እንደሚያሳውቅ መግባባት ላይ የተደረሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

56. በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ችግር፣ ያለውም ኃይል መዋዠቅ እና መቆራረጥ ምክንያት የፋብሪካዎቹ መሣሪያዎች እየተበለሹ የምርት ሂደት እንዲቆራረጥ እና የውጭ ንግድ ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ አድርጓል፡፡

## በኢንደስትሪ ዘርፍ ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራትን በተመለከተ

57. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር የሰው ኃይልን በማብቃት ለኢንደስትሪው የሚያስፈልግ የሰው ኃይል የሚሟላበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

58. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በኦዲት በታዩ ፋብሪካዎች በጨርቃ ጨርቅ እና ቴክስታይል ዘርፍ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ከኢንዱስትሪው ገሃድ አለም አሰራር ጋር የማይተዋወቁ መሆኑ፣ ይህም ማኑፋክቸሪንጉ በሚፈልገው ዲሲፕሊን ተማሪው ታንጾ የማይወጣ መሆኑ፤ የፋብሪካውን ሥርዓት እና ቴክኖሎጅ ጋር ተላምደው እንዲመረቁ የሚያስችል ሥርዓት አለመኖሩን ከኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅና አልበሳት፤ባህርዳር ጨርቃጨርቅና አልበሳትና አይካ ቴክስታይል ኃላፊዎች ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

59. ጉዳዩን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበለይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመረቁ ተማሪዎች በመጀመሪያ ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት የተግባር ልምምድ በኢንዱስትሪዎች የሚያካሂዱ መሆኑ እና ተመርቀው በኢንዱስትሪዎች ከመቀጠራቸው በፊትም በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የማሰልጠኛ ጣቢያ እና በፋብሪካዎች ሥራ ላይ ሥልጠና የሚሰጣቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘርፉ የሚፈልገውን ባለሙያ ከሚመለከተው መ/ቤት ጋር የሚነጋገር ቢሆንም ካሪኩለሙን አዘጋጅቶ ሥራ ላይ የማዋል ድርሻ የእርሱ ባለመሆኑ ጭምር የተከሰተ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

60. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ከኢንዱስትሪው ገሃድ አለም ጋር እንዲተዋወቁና ብቁ እንዲሆኑ ከዩኒቨርቲዎች ጋር በቅንጅትና በየወቅቱ በመመካከርና ክፍተቶችን በመለየት የጋራ

መፍትሄ ስለማይሰጥ የምርት መጠንና ጥራት ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

## ለኢንዱስትሪዎች የሚሰጥ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ አሰራርን በተመለከተ

61. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኤክስፖርት ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚሰጠው የተለያዩ የማበረታቻ ድጋፍ ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

62. በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጂያዊ ውጤት ቶኮር (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት የኢንዱስትሪ ምርቶች የኤክስፖርት ገቢን ለማሳደግ የኤክስፖርት ማበረታቻዎች በተፈቀዱበት አግባብ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የመከታተልና የማረጋገጥ፣ተግባራትን ማከናወን የሚል በዕቅዱ ላይ ተይዟል፡፡

63. በኤክስፖርት ምርት ማምረት ላይ የተሰማሩ ፋብሪካዎች ከውጭ ምርት ንግድ የሚያስገቡት የውጭ ምንዛሪ እና ጥሬ ዕቃ ከውጭ ለማስገባት የሚጠቀሙት የውጭ ምንዛሪ (ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ ልከው የሚያስገቡት የውጭ ምንዛሬ እና ለዚሁ ምርትን ለማምረት ከውጭ አገር ለሚያስገቡት የጥሬ ዕቃ የሚጠቀሙት የውጭ ምንዛሬ) ልዩነት/ብልጫ ሊያሳይ የሚችል እና በውጤቱ መሠረት አናሳ አፈጻጸም የሚያሳዩ ፋብሪካዎች ላይ ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግበት አሠራር ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ በተጨማሪም በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ 768/2004 ዓ.ም. መሠረት የተደነገጉት ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች ፤የተመላሽ ቀረጥ ስርዓት፤የቫውቸር ሥርዓት፤የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት፤የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት፤የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት እና የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ሲሆን እንዲሁም ማንኛውም ለወጪ ንግድ ምርት ማምረት አገልግሎት የሚውል ጥሬ ዕቃ (ግብዓት) ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር እንዲገባ ስርዓት ተዘርግቷል፡፡

64. ነገር ግን የተዘረጋው ሥርዓት ወጥ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ባለመደረጉ፡-
   - ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2007 ዓ.ም በጀት ዓመት የጥቅምት እና የሕዳር ወር የወጪ ንግድ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ ልከው የሚያስገቡት የውጭ ምንዛሬ እና ለዚሁ ምርትን ለማምረት ከውጭ አገር ለሚያስገቡት የጥሬ ዕቃ የሚጠቀሙት የውጭ ምንዛሬ ልዩነት/ብልጫ ሊያሳይ የሚችል እና በውጤቱ መሠረት አናሳ አፈጻጸም በኤም ኤን ኤስ (ክርና አልበሳት አምረች)፤ ዶንግፋንግ ስፒኒንግ፣ፐሪንቲንግዳ ይንግ ፋብሪካ (ጨርቃጨርቅና አልበሳት አምራች)ና ኢቱር ቴክስታይል ፋብሪካ ክር አምረች

ያሳዩ መሆናቸው ታውቋል፡፡

- የቴክኖ ሞባይል ማገጣጠሚያ ፋብሪካ በ2005 ዓ.ም ጥሬ ዕቃን ወደ አገር ለማስገበት በኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል ብር 113,000,000 (አንድ መቶ አስራ ሶስት ሚሊዮን ብር) በዲፖዝት እና ቫት መልክ የተያዘው እስከ አሁን ያልተሰጣቸው መሆኑን ከተከለሱት ዶክሜንቶችና ከፋብሪካው ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በኢንጀስኮ ኢትዮጵያ ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግል ማህበር ወደ ውጭ ለላከው ምርቶች (በተመላሽ ቀረጥ ስርዓት መሰረት) የቀረጥ ተመላሽ ብር 443,301.87 ብር በ17/06/2006 ዓ.ም ቅድመ ሁኔታዎቹን ያሟላ መሆኑ እየተረጋገጠ እስከ አሁን ድረስ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል ያልተከፈለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የኒው ዊንግ ጫማ ፋብሪካ ከሀገር ውጪ የሚያስገባቸው የጥሬ እቃዎች በገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል የሚሰጠው የፋሲሊቴሽን አገልግሎት በመዘገየቱና ድጋፍ ባለመሰጠቱ ምክንያት የታዛዘውን ስራ በጊዜው ባለማድረሱ በውሉ መሠረት 10% ወይም 400 ሺህ አሜሪካ ዶላር በደንበኞቻቸው የተቀጡ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከፋብሪካው ኃላፊዎች ከተደረገው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ዶንግፋንግ ስፒኒንግ፣ፕሪንቲንግ እና ዳይንግ ኃ.የተ.የግል ማህበር የተባለው በኢስተርን ኢንዱስትሪ ዞን በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ የተሠማራ የቻይና ዜግነት ያለው ባለሃብት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ 768/2004 ላይ ከተደነገጉት ሥርዓቶች ውጭ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በተጻፈለት የድጋፍ ደብዳቤዎች መሠረት ብቻ ከቀረጥ ነጻ ሁሉም ግብዓቶችንና ጥሬ ዕቃዎችን ወደ አገር እያስገባ እና ምርቱን ሙሉ በሙሉ ለሀገር ውስጥ ገበያ እያከፋፈለ መሆኑን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከተጻፈው የድጋፍ ደብዳቤዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- እንዲሁም የቻይና፣የቱርክና የህንድ ዜግነት ያላቸው ባለሃብቶች (ዶንግፋንግ፣ኢቱር ቴክስታይል እና ኤልሴ አዲስ ቴክስታል) ከተሰማሩበት አላማ ውጭ (ሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶች አምርተው ወደ ውጪ መላክ ሲገባቸው) በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ እንዲሰማሩ በተመረጡ የንግድ ስራዎች ላይ የንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው በህገወጥ መንገድ ምርቶቻቸውን እያከፋፈሉ መሆናቸውን ከተከለሱ ዶክሜንቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

65. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የአሠራር

ሥርዓቱን በተመለከተ ውጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቱ፣ ከቀረጥ ታክስ ነፃ የገቡ ጥሬ ዕቃዎች ለኤክስፖርት ብቻ ኢንዲውሉ ያስገድዳል፡፡ ለዚህም የግብዓት ምርት ጥምርታ (input-output coefficient} በመጠቀም ለወጪ ምርት መዋላቸው በየዓመቱ ተረጋግጦ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በኩል ኪሊራንስ ካልተሰጠ የሚታደስበት ሁኔታ ስለሌለ ቁጥጥሩ አለ ማለት ነው፡፡

66. የቀረጥ ተመላሽ ችግሮች ሰፊ ናቸው፡፡ የብዙዎች ችግሮች የተፈታ ቢሆንም የቀሪዎቹ የችግሩ ምንጭ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ባለሀብቶች ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ሲቀሩ እና የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የአሠራር ቅልጥፍና የሌለው በመሆኑ ገልጸዋል፡፡

67. የኒው ዊንግ ጫማ ፋብሪካ ጋር ባለን ግንኙነት መሠረት በየጊዜው የምንከታተለውና የጉምሩክ ፋሲሊቴሽንም ችግር ሲያጋጥመው ለበርካታ ጊዜያት ድጋፍ አድርገናል፡፡ ነገር ግን በውሉ መሠረት 400 ሺህ ዶላር ስለመቀጣቱ ከድርጅቱ በኩል የደረሰን ሪፖርት የለም፡፡ ፋብሪካው እነዚህ የፋሲሊቴሽን ችግሮች ስላሉበት አሁን በኮንቴይነር ተጭነው የሚመጡት ዕቃዎች የአረንጓዴ መስመር (በታማኝነት የሚፈታሹ) ተጠቃሚ በመሆኑ ግቢው ውስጥ ስለሚፈተሽ ችግሩ ተቃሏል በማለት ገልጸዋል፡፡

68. ይህ በመሆኑ ድርጅቶቹ በቀረጥ ነጻና በውጭ ምንዛሪ ያስገቡትን የፋብሪካ ግብኣቶችን ለሀገር ውስጥ ገበያ በማቅረብና ገበያውን ከመረበሽም በላይ ሀገሪቱ ከቀረጥና ታክስ ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዲያስቀር ከማድረጉም በላይ የውጭ ምንዛሬ አለአግባብ እንዲጠቀሙ በር በመክፈት ብክነትን የሚያስከትል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ ከሚመለከታቸው አከላት ጋር በመሆን መፍትሄ ባለመስጠቱ ምክንያት ፋብሪካዎቹ የስራ ማስኬጃ (working Capital) ገንዘብ እጥረት በየጊዜው እያጋጠማቸው ስለሆነ የፋብሪካዎቹ የእለት ዕለት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ ከባለድርሻ አከላት ጋር በመወያየት ወቅታዊ እና ዘለቄታዊ መፍትሄ ስለማይሰጥ ፋብሪካዎቹ በፋሲሊቴሽን ችግር ምክንያት ላልተፈለገ ወጪ እንዲጋለጡ ከማድረጉም ባለይ ሀገሪቱ ልታገኝ የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ እንድታጣ እያደረገ ይገኛል፡፡

69. ጉዳዩን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ዶንግፋንግ የተባለ የቻይና ኩባንያ ለምርት ተግባር ያስመጣቸው ግብዓቶች ለማስገባት ባለመቻሉ ከፍተኛ ችግር ያጋጠመው በመሆኑ ጂቡቲ ወደብ የሚገኙ እና እየመጡ ያሉ እንዲሁም ኤርፖርት የሚገኙ ዕቃዎችን ለማስገባት የድጋፍ ደብዳቤ እንዲጻፍለት በጠየቀው መሠረት መስሪያ ቤታችን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደብዳቤ ጽፎ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርም በውሉ ላይ የሚነሱ አለመግባባቶች እልባት እስኪያገኙ ወደፊት ቀረጥ እና ታክስ እንዲከፍል የሚወሰንበት ከሆነ ለመክፈል ግዴታ በመግባት ጥሬ ዕቃዎችን ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲያስገባ መፍቀዱን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ደብዳቤ መጻፉን፣ በወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ በሆኑና ግዴታቸውን ባልተወጡ ኩባንያዎች ላይ በቀረጥ ማበረታቻ አዋጅ መሠረት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ውሳኔ ተላልፏል፡፡ የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው በህገወጥ መንገድ ምርቶቻቸው እያከፋፈሉ ስለመሆናቸው መረጃው የሌላቸው እና በፈቃዳቸው ልክ ስለመሥራታቸው የሚቆጣጠራቸው ፈቃዱን የሰጣቸው አካል እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፤ በማለት ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማበረታቻ ሥርዓቱን ተጠቅሞ በህጉ መሰረት በዓመት ውስጥ ምርቱን ወደ ውጭ ካላከ ቀረጡን ከሃምሳ ከመቶ መቀጫ ጋር እንዲከፍል ብቻ የሚገደድ በመሆኑ ይህን እከፍላለሁ ካለ ምንም ማድረግ እንደማይቻል በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

70. ለወጭ ንግድ ማስፋፊያና ማበረታቻ ተብለው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ግብዓቶችንና ጥሬ ዕቃዎችን ተጠቅመው ያመረቱትን ምርት ሙሉ በሙሉ ለሀገር ውስጥ ገበያ ማዋላቸው ቀረጥና ታክስ ከፍለው በተመሳሳይ ሥራ ላይ የተሰማሩ ህጋዊ የሆኑ ሌሎች አምራች ድርጅቶች መካከል ልዩነት እንዲኖርና ፍትሃዊ የገበያ ውድድር እንደይኖር በማድረግ የሀገር በቀል እንዱስትሪዎችን እድገት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር እና ሀገሪቱ ልታገኝ የሚገባውን ከታክስና ቀረጥ ገቢ ላይ እና የውጭ ምንዛሪ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

## በወጪ ምርት ለተሰማሩ ፋብሪካዎች የጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ጥራትን በተመለከተ

71. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኤክስፖርት ስራ ጋር በተያያዘ በጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ግብይት ስርዓት ላይ ለአምራች ላኪዎች የተለያዩ ከግብአት አቅርቦት ጋር በተያያዘ አቅም ግንባታ ድጋፎች መስጠት ይገባል፡፡

72. በኢንዳስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጂያዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ 2004-2007 ዓ.ም ላይ በምርትና ግብዓት ቅብብሎሽ ሰንሰለት ላይ የሚያጋጥሙ የአሰራር ችግሮችን በጥናትና ምርምር በመፍታት፣በጥቃቅን፣ አነስተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተሳለጠ የግብዓትና ምርት ትስስር እንዲሁም የከፊል-ኮንትራታዊ ቁርኝት እንዲኖር ሙያዊ ድጋፍ መስጠት ነው የሚል ተቀመጧል፡፡

73. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቆዳ የኤክስፖርት ዘርፍ የሚፈለገውን ውጤት

ለማስመዝገብና በአለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቀጠል የቆዳ ጥራት የሚሻሻልበትና ምርታማነቱ የሚጨምርበት ስልት ለመንደፍ እና ትኩረት እንዲሰጥ ከግብርና ሚኒስቴርና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ቢኖርም በቂ እና ውጤታማ አለመሆኑ ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንስቲትዩት ሥራ ኃላፊዎች በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችላል፡፡

74. እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በኦዲት ወቅት በታዩ ቆዳ የኤክስፖርት ዘርፍ ላይ የተሠማሩ ፋብሪካዎች ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ፤ኒው ዊንግ ጫማ ፋብሪካ አ.ማ እና የአንበሳ ጫማ አ. ማህበር የጥሬ ዕቃ አቅርቦት (ቆዳና ሌጦ) እጥረት ምክንያት በእቅዳቸው የተያዘውን የምርት መጠን ማምረትና ለአለም ገበያ መቅረብ አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ከተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

75. ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጥረቱ አለ ነገር ግን ውጤታማ አልሆነም፡፡ የጥሬ ቆዳ እና ሌጦ ጥራትን በተመለከተ አንድ የግብርና ግብአት በመሆኑ እንስሳው በህይወት እያለ ጀምሮና ከታረደም በኋላ ቆዳው ታሽጎ ወደ ፋብሪካ እስኪደርስ ያለው የጥራት አጠባበቅ ስራ የግብርና በመሆኑ ስልቱንም መንደፍ ያለበት (ግብርና ሚኒስቴር ) እነደሆነና ችግሩ ለመቅረፍ ከግብርና ጋር የጋራ ዕቅድ መኖራቸው፡፡ በዕቅዱ መሠረት መስራቱም በየጊዜው በጋራ የሚገመገም መሆኑንና ጥሬ ቆዳና ሌጦው ጥራት እንዲጠበቅ ቅንጅታዊ አሰራሩን ውጤታማ ለማድረግ ይሰራል ቢሉም የጋራ ዕቅዱን የሚያሳይ መስረጃ መቅረብ አልተቸለም፡፡

76. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን ይበል እንጅ የጥሬ ቆዳ እና ሌጦ ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች እንዱስትሪ ዘርፍ ዋና ግብዓት በመሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ከግብርና ሚኒስቴር እና ሌሎችም ባለድርሻ አከላት ጋር የጋራ ስምምነት በመፍጠር በተቀናጀ መልኩ የቆዳ ጥራት የሚሻሻልበትና ምርታማነቱም የሚጨምርበት የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ስልት ባለመንደፉ ምክንያት በቆዳ እንዱስትሪ ምርት በአለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቀጠል አላስቻለውም፡፡

77. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ክፍሉ ኃላፊዎች ጉዳዩን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ያልተቻለበት ዋና ምክንያት፣ በከብት ቆዳ ላይ የብዛት ችግር የሌለ ቢሆንም የጥራት ችግር ግን ጎልቶ ስለሚታይ ችግሩን ከግብርና ሚ/ር ጋር በመሆን ለመቅረፍ ስራዎች እየተሰሩ የሚገኙ ቢሆንም በልጦ የሚታየው ችግር ግን የመጠንም የጥራትም ችግር ሰላለ ከውጭ በማምጣት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

78. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በግብዓት አቅርቦት ትስስርን

በተመለከተ የቆዳ ኤክስፖርት ምርት አምራች ኩባንያዎች መካከል የአሠራር ስርዓት እንድፈጠርና ተግባራዊ ባለመደረጉ ምክንያት የታለመውን አላማ ግብ ለማድረስ አልተቻለም፡፡

## ለፋብሪካዎች የግብዓት አቅርቦት ትስስርን በተመለከተ

79. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ አገር ውስጥ ገቢ ምርቶችን የሚተኩ የአገር ውስጥ ምርቶች ለገበያ ተደራሽ እንዲሆኑ የግብይት ስትራቴጂ መንደፍና ስራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡

80. በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጂያዊ ውጤት ተኮር (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት ገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የውጭ ምንዛሪ ለማዳን እና የኢንዱስትሪውን መሠረት ለማስፋት ከፍተኛ ድርሻ ስላላቸው የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲስፋፉ ዕቅድ ተይዟል፡፡

81. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡት ፋብሪካዎች ማካከል በአይካ አዲስ ጨርቃጨርቅ፤ባህርዳር ጨርቃጨርቅ አ.ማ እና ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ የጥጥ አቅርቦት እጥረት በተዳጋጋሚ የሚከሰትና ያለውም ጥጥ ጥራት ጉድላት ያለውና የአለም ገበያ ያገናዘበ ባለመሆኑ ፋብሪካዎቹ ከሀገር ውጭ በውጭ ምንዛሪ እያስገቡ መሆኑን በፋብሪካዎቹ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፤

82. በጉዳዩ ላይ የሚመለከተው የሥራ ክፍል ተጠይቀው በሰጡት መልስ የጥጥ ምርት ግብዓት እጥረት በመጠንም ሆነ በጥራት መጉደል ይከሰታል፡፡ ሆኖም ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግሩን በዝምታ ሊያየው ስላልፈለገ የተለያዩ አማራጮችን በማፈላለግ ለመቅረፍ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የግብዓት አቅራቢዎች ኮርፖሬሽን በማቋቋም የግብዓት እጥረት እንዳይከስት ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

83. የግብዓት አቅርቦት ትስስር በአምራቾችና በተጠቃሚዎች መካከል አለመኖሩና በሚፈለገው ጥራትና ጊዜ አለመቅረቡ የግብዓት እጥረት በመጠንም በጥራትም እንዲከሰት በማድረግ በወጪ ንግድ ምርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

## ለወጪ ምርት ለማሳደግ የጥናትና ምርምር ሥርፀት ሥራዎችን በተመለከተ

84. ሚ/ር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ለዘርፉ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምርና ሥርፀት ሥራዎችን ማካሄድ ይገባል፡፡

85. የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 181/2002 ዓ.ም መሠረት ለኢንስቲትዩቱ የተሰጠው ተግባር የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤

ከዩኒቨርስቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ይሰራል፤ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር እንደሚያግዝ ይደነግጋል፡፡

86. በዚህም መሠረት የጨቅርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 180/2002 ዓ.ም መሠረት ለኢንስቲትዩቱ የተሰጠ ሥልጣንና ተግባር መካከል፤ ለዘርፉ ድጋፍ የሚያደርጉ የምርምር ተቋማትን፤ዩኒቨርሲቲዎችን፤ የጥጥና የጨርቃጨርቅ አምራች ማህበራትን እና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማቀናጀት በዘርፉ ችግሮች ላይ ምርምሮች ማካሄድና የምርምር ውጤቶቹ ሲጸድቁ ተግባራዊ እንዲያደርግ ተቋቁሟል፡፡

87. ይሁን እንጂ በሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ ኢንስቲትዩቱም የወጪ ንግድ ምርት ላይ ለተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ላይ ዘርፉን የሚመለከት እና ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ለማከናወን ከሚመለከተቸው አካላት ጋር በመተባበር በሁሉም ዘርፎች የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ተግባራዊ መሆናቸውን የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራው ክፍሉ ኃላፊዎች መስረጃ ተጠይቀው መቅረብ አለመቻለቸውን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም አሸራፍ ኃላ.የተ.የግል ማህበር ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የኦዲት ሪፖርቱ እስከ ተጠናቃቀ ድርስ ምርት እያመረተ አለመሆኑ እየተወቀ እስከ አሁን ፋብሪካው ወደ ምርት ለመመለስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተደረጋው ድጋፍና ችግሩን ለመፍታት የተከሄደው ጥናት አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

88. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ጉዳዩን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤የክትትል ሥርዓት ከተዘረጋ ዓመታት አልፈዋል. ይህ ከላይ ጀምሮ በብሄራዊ ኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ፣በሚኒስቴሩ የበላይ አመራር፣ ኢንስቲትዩቶች፣ የልማት ቡድኖችና ግለሰብ፣ ባለሙያዎች ይከናወናል ቢሉም የተከናወኑ ጥናቶች ተጠይቀው መቅረብ አልተቻለም፡፡

89. በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በኢንስቲትዩቶቹ ከሚመለከተው አከላት ጋር በመሆን ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶች ባለመከናወኑ የዘርፎቹን ችግሮች ለመፍታትና የተሻለ አማራጮች ሥራ ላይ እንዳይውሉ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

90. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ጥናት መደረጉን ከባለ ድርሻ አካላት የተውጣጣ የባለሙያዎች ቡድን ጉብኝት ማድረጉን፣ ባለሙያዎቹ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠርተው መጠየቃችውን፤ የማሳሰቢያ ደብዳቤም በኢንቨስትመንት ኤጀንሲ መጻፉን፣ በጠቅላላው በቂ ክትትልና ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን እምነት አለኝ ቢሉም ጥናት የተደረገበት ማስረጃ ለኦዲት ሊቀርብ ስላልቻለ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

91. በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በኢንስቲትዩቶቹ ከሚመለከተው አከላት ጋር በመሆን ችግር

ፊቺ የሆኑ ጥናቶች ባለመከናወኑ የዘርፎቹን ችግሮች ለመፍታትና የተሻለ አማራጮች ሥራ ላይ እንዳይውሉ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋብሪካውን ችግር ለመፍታት ጥናት በማድረግ የችግሮቹን መንስኤ ምን እንደሆነ በማወቅ እና ለችግሮቹ መፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ ባለመቻሉ አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ባለመቻሉ ፋብሪካው ለሦስት ዓመታት ምን እየሰራ እንደሆነ ያልታወቀ መሆኑን ወደ ውጭ ያልላከ መሆኑን እና ለማወቅ ተችሏል፡፡ እስከ ኦዲቱ ወቅት ድረስም ወደ ምርት ማምረት ያልተመለሰ መሆኑንም ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

## ለወጪ ንግድ ማምረት የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግን በተመለከተ

92. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በግብይት ዙሪያ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት የአምራች ድርጅቶችን የኤክስፖርት ገበያ የመድረስ አቅማቸውን ለመገንባት ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንዑስ ዘርፎቹን ለመደገፍ የተቋቋሙትን ኢንስቲቲዩቶች ከሌሎች ዓለም ዓቀፍ ዕውቅናና ብቃት ካላቸው ተቋማት ጋር በማቆራኘት አቅማቸውን በዘላቂነት የሚገነባበት ስርዓት መዘርጋት ይገባል፡፡
93. በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጅያዊ ውጤት ተኮር እቅድ (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት የኢንዱስትሪ ዘርፉን ለመደገፍ የፈፃሚውን ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ የሚያስችሉ የትምህርት፣ የሥልጠና እና የልምድ ልውውጥ በማካሄድ፣ በራስ የመተማመንና ችግር የመፍታት ብቃትን ማጎልበት ዕቅድን አካቷል፡፡
94. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኢንጀስኮ ኢትዮጵያ፣ በአይካ አዲስ ቴክስታይል፤ በቤዛ ኢንዱስትሪ፤ በኒው ዊንግ ቆዳ ፋብሪካ፣ በቴክኖ ሞባይል ማገጣጠሚያ ፋብሪካ፤ በደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካ፣ በኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ የኢንዱስትሪዎቹ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ሥልጠናዎችን (በቴክኒክ፤ በሥራ አመራርና በግብይት ዙሪያ) ክፍቶች በሚታይባቸው ሙያዎች ዳሳሰ ጥናት በማድረግ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በዘርፉ በተቋቋሙ ኢንስቲትዩቶቹ በኩል በቂ ሥልጣና የማይሰጥ መሆኑን በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡
95. ለሌሎች ፋብሪካዎች የሚሰጥም ስልጠናም ቢሆንም በኤክስፖርት ምርት መጠን፤ጥራት እና የኤክስፖርት እቅድ አፋጻጸም ላይ ያስገኘው ጠቀሜታ/ ፋይዳ የማይገመገም መሆኑን ከተደረገው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንዑስ ዘርፎችን ለመደገፍ የተቋቋሙት የኢንስቲትዩቶችን አቅም ለማጎልበት ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ

የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር በመፍጠር ለኢንዱስትሪዎች የቴክኒክ ድጋፍ በጋርመንት እና በግብይት የሥራ መስኮች ብቻ በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ የተሰጠ ሲሆን በሌሎቹ መስኮችና ኢንዱስትሪዎች ያልተሰጠ መሆኑን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት 2006 ዓ.ምና የ2007 በጀት አመት የጥቅምትና የሕዳር ወር እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

96. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ጉዳዩ ላይ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አብዛኞቹ የተጠቀሱት ኩባንያዎች የውጭ አገር ኩባንያዎች በመሆናቸውና የራሳቸውን አቅም ይዘው እንደሚመጡ ይጠበቃል፡፡ ከእነርሱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በመሆናቸው የክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ይዘው እንዲመጡ የሚጠበቅ ሲሆን የሚጠቀሙትም ቴክኖሎጂዎች ከሚኒስቴር መ/ቤቱም አቅም በላይ በመሆናቸው እንደዛም ሆኖ አብዛኛዎቹ የተጠቀሱት ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡ በሌሎች የአገር በቀል ኩባንያዎች ግን የከይዘን ሥራ አመራር ተግባራዊ የተደረገና የሥልጠናውን ፋይዳ የተገመገመ ቢሆንም ለአገር ውስጥ ባለሀብት መስጠት የሚገባውን ያህል ድጋፍ እንዳልተሰጠ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በኤክስፖርት ምርት መጠን፣ ጥራት እና የኤክስፖርት እቅድ አፋጻጸም ላይ ያስገኘው ጠቀሜታ/ ፋይዳ የተገመገመበት ማስረጃ ኦዲቱ አስከተጠናቀቀበት ድረስ አልቀረበም፡፡

97. የዘርፎቹን አቅም ለመገንባት ተመሳሳይ የሆኑ ተቋማት ቁርኝት በቆዳ ዘርፍ ከሕንድ መርሐ ግብር በዝርዝር ጥናቱ ተነስቶ ተግባራዊ መሆኑና በጨርቃጨርቅ ዘርፍ ከሕንድ ያለው ተቋማት ጋር ፕሮግራም የተጀመረ ሲሆን በተመሳሳይም የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አቅም ለመገንባት በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

98. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንዱስትሪዎቹ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ሥልጠናዎችን (በቴክኒክ፣ በሥራ አመራርና በግብይት ዙሪያ) ባለመስጠቱ የፋብሪካዎችን ምርት እና ምርታማነት በጥራትም በመጠንም ለመጨመር ፣በየጊዜው የሚከሰቱትን የፋብሪካዎች የአመራር ችግሮችን ለመፍታት እና የደንበኞችን አያያዝ ለማሻሻል አልተቻለም፡፡

## ለወጪ ምርቶች የገበያ መረጃ እና ድጋፍን በተመለከተ

99. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ ምርቶችን በአለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ ወደ ተለያዩ የገበያ መዳረሻዎች መግባት የሚያስችል የግብይት ስትራቴጂ መንደፍና ስራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡

100. በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጅያዊ ውጤት ተኮር እቅድ (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት

በመሥራት ለኢንዱስትሪ ምርቶች የገበያ አድማስ ማስፋት፣ ኢንቨስትመንትን መሳብና ፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግርን የማረጋገጥ ዕቅድ ተይዟል፡፡

101. ይሁን እንጂ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አዳዲስ የመዳረሻ ገበያዎችን ለማፈላለግና በስፋት የኢንደስትሪ ምርቶችን ለአለም ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የጋራ መግባበያ በመዘጋጀት እና የገበያ ማስፋፋት ስትራቴጅ በመቅረጽ በውጭ አገር ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በኩል ተግባራዊ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከፋብሪካዎች ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

102. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በንግድ ሚ/ር ሰብሳቢነትና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጸሀፊነት የሚካሄድ የጋራ የኮሚቴ ስብሰባና ውይይት የሚደረግበት የውጭ ንግድ የሚስፋፋበት፣ከውጭ ሚሲዮኖቻችን ግንኙነት የሚደረግበት አሰራር አለ፡፡ ግን በየወቅቱና በበቂ ደረጃ ይደረጋል የሚል እምነት የለንም፡፡ ዕቅድም ይዘጋጃል አፈጻጸሙም ይገመገማል በሚፈለገው ሁኔታ ግን እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

103. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዓለም አቀፍ የገበያ መዳረሻዎች ላይ ጥናት በማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አከላት ጋር በጋራ የገበያ ማስፋፋት ስትራቴጅ በመቅረጽ ተግባራዊ ባለመድረጉ ምክንያት እንዱስትሪዎች የገበያ መፋላለግ አቅምና ልምድ ባለመኖራቸው ምርቶቻቸውን ለአለም ገበያ በስፋት ተወዳዳሪ ሆኖ መቅረብ ስላልቻሉ ወደ ሀገር ውስጥ ገበያ እንድያዘነብሉ ከፍተኛ አስተወጽኦ አድርጎል፡፡

# ክፍል ሦስት

## *መደምደሚያ*

104. በኢንዱስትሪ ምርቶች ኤክስፖርት (የወጪ ንግድ) በናሙና ተመርጠው በኦዲት በታዩ ፋብሪካዎች ምርት የወጪ ምርት ንግድ አፈጻጸም ሲገመገም የሚከተሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኤክስፖርት ስትራተጂክ ዕቅዱን ሲያዘጋጅ ወሳኝ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር እና በመቀናጀት በዝርዝር ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ (የወጪ ምርት) ኤክስፖርት እቅድ ሲያዘጋጅ በዘርፉ ከተሠማሩ ባለሃብቶች ጋር በመቀናጀት ከጥሬ ዕቃ አቅርቦት ጀምሮ እስከ ምርት ማምረት እና ለአለም ገበያ መሸጥ ድረስ ያለውን የአሰራር ክፍተቶችን በየዘርፎቹ በመለየት ለችግሮቹ የመፍትሄ አቅጣጫ አስቀድሞ በማስቀመጥና በመካላከልና ችግሮቹ በሚከሰቱበት ወቅትም አፋጣኝ ምላሽ/እ ርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ አለመዘጋጀቱ፣
- የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት የወጪ ንግድ አፈጻጸም፣የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የውጪ ምርት ንግድ ዕቅድ አፈጻጸም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2005ዓ.ም. እና በ2006 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሪፖርት ጋር ልዩነት ያለው መሆኑ፣ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በኦዲት ከታዩት ፋብሪካዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በፋብሪካዎች የሚቀርበው የወጪ ምርት ንግድ አፈጻጸም የተለያየ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኤክስፖርት ዕቅድ ሲያዘጋጅ የሚመለከታቸው ወሳኝ ባለድርሻ አካላትን ጋር በመሆን እቅድ አፈጻጸሙ ላይ ሰፊ ውይይት ተደገርጎበት ለኢንስቲትዩቶችና ለፋብሪካዎች የግምገማ ሪፖርት /ግብረ መልስ በመላክ ክትትልና ድጋፍ በወቅቱ ባለመደረጉ በየጊዜው የሚከሰቱ ችግሮች ወቅታዊ መፍትሄ ማግኘት አለመቻላቸው፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ (ኤክስፖርት ዘርፍ) በተመለከተ በአንድ ማዕከል የተደራጀ የመረጃ አገልግሎት ሥርዓት ያልተዘረጋና ተግባራዊ ያልሆነ በመሆኑ ወቅታዊ፣ትክክለኛ፣ የተሟላና የተደራጀ መረጃ ለሚመለከታቸው የዘርፉ ተጠቃሚዎች በተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲያገኙ አለመደረጉ፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀምና ለዘርፍ ተጠቀሚዎችን በማስተዋወቅ አግባብ የሆኑ መረጃዎችን (ምርጥ ተሞክሮዎች፣ የምርምርና ስርፀት ውጤቶች፣ አዳዲስ የለውጥ መሳሪያዎች፤የግብይት እና የመሳሰሉት)፤በማዕከል በማደራጀት ወቅታዊ፣ የአለም አቀፍ እና የተሟሉ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን በየጊዜው

በማሰባሰብ፣ በማጠናከርና በመተንተን ለሚመለከታቸው ፋብሪካዎች በየጊዜው ተደራሽና የማይሰራጭ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዘርፎቹ የመሠረተ ልማት በተለይም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲስፋፋ ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አከላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በሚፈለገው ደረጃ ባለመሆኑ ለፋብሪካዎቹ በቂ ድጋፍ ባለመደረጉ ለአንዳንድ ፋብሪካዎች የሃይል አቅርቦት ዕጥረት፣የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና መዋዥቅ የሚታይ መሆኑና ችግሩ አለመፈታቱ ፣
- በኦዲት በታዩ ፋብሪካዎች በጨርቃ ጨርቅ እና ቴክስታይል ዘርፍ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ከኢንዱስትሪው ገሃድ አለም አሰራር ጋር የማይተዋወቁ መሆኑ፣ ይህም ማኑፋክቸሪንጉ በሚፈልገው ዲሲፕሊን ተማሪው ታንጾ የማይወጣ መሆኑ፤ የፋብሪካውን ሥርዓት እና ቴክኖሎጂ ጋር ተላምደው እንዲመረቁ የሚያስችል ሥርዓት አለመኖሩ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ የተሰማሩት ባለኃብቶች ለማበረታታት ጥሬ ዕቃን ወደ አገር በሚያስገቡበት ወቅት የቀረጥ ማበረታቻ ተጠቀሚ እንዲሆኑ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በመመካከር በወቅቱ ለተጠቀሚዎች የቀረጥ ተመላሽ እንዲሆን ባለማድረጉ የኩባንዎች/የፋብሪካዎች ገንዘብ ለረጅም ጊዜ እንዲያዝና ኢንዱስትሪዎቹ የሥራ ማስኬጃ (Working Capital) እጥረት እንዲያጋጥማቸው ምክንያት መሆኑ ፣
- የውጭ ዜግነት ያላቸው ባለሃብቶች ከተሰማሩበት አላማ ውጭ ሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶች አምርተው ወደ ውጪ መላክ ሲገባቸው በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ እንዲሰማሩ በተመረጡ የንግድ ስራዎች (በአገር ውስጥ አምርቶ መከፋፈል) ላይ የንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው በህገወጥ መንገድ ምርቶቻቸውን እያከፋፈሉ መሆናቸውን፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ 768/2004 ዓ.ም ባልተከተለ መልኩ ለውጭ ባለሀብት (ዶንግፋንግ ስፒኒንግ፤ፕሪንቲንግ እና ዳይንግ ፋብሪካ) ከቀረጥ ነጻ ሁሉም ግብዓቶችንና ጥሬ ዕቃዎችን ወደ አገር እንዲያስገባና እና ምርቱን ኤክስፖርት ማድረግ ሲገበው ሙሉ በሙሉ ለሀገር ውስጥ ገበያ እያከፋፈለ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ንግድ ምርት ማምረት ላይ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች የሚሰጠው የማበረታቻ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑና አፈጻጸሙ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበትና በመተባበር በየወቅቱ አብሮ የማይሰራና ለዘርፍ የሚሰጥ ማበረታቻ ድጋፍ ያስገኘው ውጤት የማይገመገም እና የማይታወቅ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ንግድ ምርት ላይ ለተሠማሩ አምራቾች የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር ዘለቀታዊ ማፍትሄ ለመስጠት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዝርዝር ጥናት በማካሄድ እና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ችግሩ እንዲቃለል ባለመደረጉ ምርትና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳዳሩም በላይ አንዳንድ ፋብሪካዎች (አሸራፍ ቂራ ) በዚህ ምክንያት ምርት ማምረት እንዲያቆሙ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንዑስ ዘርፎችን ለመደገፍ የተቋቋሙት ኢንስቲትዩቶችን ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር መሰል ተቋማት ጋር ተመሳሳይ ትብብር የሚደረግበት አሰራር በተወሰነ የሥራ መስኮች ብቻ ከሕንድ ተቋማት ጋር በጨርቃጨርቅ ዘርፍ ትስስር ቢኖርም በሁሉም የሥራ ዘርፎች ቁርኝት ፣ ትብብር እና ልምድ ልውውጥ አለመኖሩ ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ባለማፍጠሩ ምክንያት ለዘርፉ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምርና ሥርፀት ሥራዎችን በሁሉም ዘርፎች ላይ በማካናወን ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንዱስትሪዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ሥልጠናዎችን (በቴክኒክ፤ በሥራ አመራርና በግብይት ዙሪያ) ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ክፍተቶችን በመለየት እንደ አስፈላጊነቱ ሥልጠና የማይሰጥና የሚሰጡ ሥልጠናዎችም ቢሆን ያመጣው ፋይዳ የማይገመገም መሆኑ፣
- ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የወጪ ንግድ ላይ ለተሠማሩ የፋብሪካዎቹን የግብይት አቅም ለማጎልበት እና የኤክስፖርት ምርት ለማሳደግ ፋብሪካዎቹ (የሀገር በቀል ባለሃብቶች ከውጭ ባለሃብቶች አምራቾች) እርስ በራሳቸው እንዲማማሩ የልምድ ልውውጥ መድረክ የማይማይዘጋጅ መሆኑ፣
- በውጭ አገር ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በኩል አዳዲስ የመዳረሻ ገበያዎችን ለማፈላለግና በስፋት የእንዱስትሪ ምርቶችን ለአለም ገበያ ለማቅረብ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ቋሚ ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ ደጋፍ የማይሰጥ መሆኑ፣

ናቸው፡፡

ስለሆነም ከላይ የተገለጹትን በኢንደስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ አፈጻጸም ላይ የታዩትን ጉድለቶችን ለማስወገድ ወይም ለማስተካከል ይረዳሉ ብለን ያስብናቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

105. በኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ አፈጻጸም ላይ አፈጻጸሙን በተመለከተ የዘረጋው የአሠራር ስርዓት በቅልጥፍና ፣ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወኑ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኤክስፖርት ዕቅድ ሲያዘጋጅ ከኢንስቲትዩቶች፣ ከባለሃብቶቹ እና መንግሥታዊ የሆኑ ወሳኝ ባለድርሻ አካላትን ጋር በመመካከር እና በመቀናጀትና በጥናት ላይ የተመሠረተ ዝርዝር እቅድ ማዘጋጀት እና ተፈጻሚ ማድረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኤክስፖርት እቅድ ሲያዘጋጅ  በዘርፉ ከተሠማሩ ባለሃብቶች ጋር በቅንጅት ከጥሬ ዕቃ አቅርቦት ጀምሮ እስከ ምርት ማምረት እና ለአለም ገበያ መሸጥ ድረስ ያለውን የአሰራር ክፍተቶችን በየዘርፎቹ በመለየት ለችግሮቹ የመፍትሄ አቅጣጫ አስቀድሞ በማስቀመጥና ለመካለከልና ችግሮቹ በሚከሰቱበት ወቅትም አፋጣኝ ምላሽ/እርምጃ መውሰድ አለበት፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርብ የፋብሪካዎች የወጪ ምርቶች እቅድ አፈጻጸም ከፋብሪካዎቹ እና ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን  ጋር የሚታየውን ልዩነት በማስታረቅ ትክክለኛ ከውጭ ምንዛሪ አገሪቱ የገባቸው ገቢ እንዲታወቅ ሁሉም መረጃቸው አንድ አይነት የሚሆንበት አሰራር ዘርግቶ ለሚመለከተው አካል አንድ አይነት ሪፖርት መቅረብ አለበት፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የእክስፖርት ዕቅድን  የሚመለከታቸው ወሳኝ ባለድርሻ አካላትን በዝርዝርና በጋራ በማዘጋጀት እና እቅድ አፈጻጸሙንም በመገምገም በጋራ ለፋብሪካዎች የግምገማ ሪፖርት /ግብረ መልስ በመላክ ክትትል ማደረግ አለበት፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ (ኤክስፖርት ዘርፍ) በተመለከተ  መረጃዎችን በአንድ ማዕከል በማደራጃት የመረጃ አገልግሎት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግና ወቅታዊ፣ትክክለኛና የተሟላና የተደራጀ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው የዘርፉ ተጠቀሚዎች በተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀምና ለዘርፍ ተጠቀሚዎችን በማስተዋወቅ አግባብ የሆኑ መረጃዎችን (ምርጥ ተሞክሮዎች፣ የምርምርና ስርፀት ውጤቶች፣ አዳዲስ የለውጥ መሳሪያዎች፤የግብይት እና የመሳሰሉት)፤በማእከል በማደራጀት ወቅታዊ፣ አለም አቀፍ እና የተሟሉ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን  በየጊዜው በማሰባሰብ፣

በማጠናከርና በመተንተን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና ፋብሪካዎች የሚያገኙበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ፤ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዘርፎቹ  የመሠረተ ልማት አገልግሎትን በተለይም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እና የመሳሰሉትን አቅርቦት የሚያገኙበትን፣ ኃይል እንዳይቋረጥ እና በተፈለገው መንገድ እንዲቀርብ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አከላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የሃይል አቅርቦት ዕጥረት ለመፍታት ለፋብሪካዎቹ በቂ ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ  ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከሚመለከተቻው አካላት ጋር በመተባበርና በየጊዜው በመወያየት፤የኢንዱስትሪ መለማመጃ ሥራዎችን (workshop) በማስፋፋት ለኢንደስትሪዎች የሚያስፈልግ ብቁ የሰው ኃይል የሚያፈራበት አሰራር ሥርዓት በመፍጠር ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወጡ ተመራቂዎች ከሥራው ሁኔታና የኢንዱስትሪው ባህሪ ጋር እንዲተዋወቁ መደረግ አለበት፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ የተሰመሩት ባለኃብቶች ለማበረታታት ጥሬ ዕቃን ወደ አገር በሚያስገቡበት ወቅት የቀረጥ ማበረታቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በመመከካር ለተጠቃሚዎች የቀረጥ ተመላሽ ገንዘብ በወቅቱ እንዲመለስላቸው በማድረግ ኢንዱስትሪዎች የሥራ ማስኬጃ (Working Capital) እጥረት እንዳያጋጥማቸው ማድረግ አለበት፤
- የውጭ ዜግነት ያላቸው ባለሃብቶች ከተሰማሩበት አላማ ውጭ (ሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶች አምርተው ወደ ውጪ መላክ ሲገባቸው) በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ እንዲሰማሩ በተመረጡ የንግድ ስራዎች ላይ የንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው በህገወጥ መንገድ ምርቶቻቸውን እንዳይከፋፈሉ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ መወሳድ አለበት፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ 768/2004 ዓ.ም በተከተለ መልኩ ለውጭ ባለሀብት ከቀረጥ ነጻ ሁሉም ግብዓቶችንና ጥሬ ዕቃዎችን ወደ አገር እንዲያስገቡና ምርቱን ኤክስፖርት እንዲያደርጉ በማድረግ የሀገሪቱን ህግ በማስከበር ፍትሃዊ የገበያ ውድድር እንዲኖርና ሀገር በቀል አምራች ድርጅቶች በማበረታታት ሀገሪቷ ከቀረጥና ታክስ ገቢ እንዲታገኝ ማድረግ አለበት፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፋብሪካዎች የሚሰጠው የማበረታቻ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑና በአፈጻጸሙ መሠረት ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል አሰራር  ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመዘርጋት ለዘርፍ የሚሰጥ ማበረታቻ ድጋፍ  ያስገኘው ውጤትን ማረጋገጥ አለበት፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርትና ምርታማነት ለመጨመር የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር ዘለቄታዊ በሆነ መልኩ መፍትሄ ለመስጠት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዝርዝር ጥናት በማካሄድ ከበለድርሻ አካለት ጋር ስምምነት ሊኖርና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንዑስ ዘርፎችን ለመደገፍ የተቋቋሙት ኢንስቲትዩቶች አቅም ለማጎልበት ተመሳሳይ አላማና እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ ዕውቅናና ብቃት ካላቸው ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር በሁሉም የሥራ መስኮች በሚፈለገው መጠን ድጋፍ በመስጠት ምርትና ምርታማነትን በጥራትና በመጠን ለውጥ ማምጠት አለበት፤
- ሚ/ር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠርና የጋራ ስምምነትን በማዘጋጀት ለዘርፉ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምርና ሥርፀት ሥራዎችን በሁሉም ዘርፎች ላይ ማከናወን አለበት፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየንዑስ ዘርፉ በተቋቋሙ ኢንስቲትዩቶች በኩል የኢንዱስትሪዎችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ሥልጠናዎችን (በቴክኒክ፤ በሥራ አመራር፤በግብይት ዙሪያና በሌሎችም) ዳሰሰ ጥናት በማካሄድ ክፍቶችን በመለየት ሥልጣና መስጠት አለበት፤የሚሰጥ ስልጠናም የሚያመጣው ፋይዳ መገምገም አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ላይ ለተሠማሩ የፋብሪካዎቹን የዕውቀትና የቴክኖሎጅ ሽግግር በማድረግ የግብይት አቅም እንዲያጎለብቱ እና የኤክስፖርት ምርት ለማሳደግ አምራቾቹ እርስ በራሰቸው እንዲማማሩ የልምድ ልውውጥ መድረክ ማዘጋጀት አለበት፤
- ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አዳዲስ የመዳረሻ ገበያዎችን ለማፋላለግና በስፋት የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለአለም ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ ሊያዘጋጅ እና የገበያ ማስፋፋት ስትራቴጅ በመቅረጽ በውጭ አገር ከሚገኙ የእትዮጵያ እምባሲዎች በኩል ተግባራዊ ማድረግ አለበት፤

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የኢንስቲትዩቶች፤ የፋብሪካዎች ኃላፊዎችና ሰራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

## የኦዲት አካባቢ ፦ የኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ አፈፃፀምን

| የኦዲት ጭብጦች<br>(Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. ሚ/ር መ/ቤቱ የጥናትና ምርምር ተግባሮችን ማከናወንና የአቅም ግንባታ ስራዎችን አቀናጅቶና አሟልቶ መተግበሩን መገምገም፣<br>1.1 ሚ/ር መ/ቤቱ ማሰልጠኛ ተቋማትን እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኢንደስትሪ ወጪ ምርት ላይ ጥናት እና ምርምር እና ለኢንደስትሪ ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣ | 1. ሚ/ር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ምርት ላይ ለተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ላይ ምርምር ሥርፀት የሚያካሂዱ ተቋማት ማስፋፋት አለበት:: |
| | 2. ሚኒስትር መ/ቤቱ የኢንደስትሪ ልማት ማሰልጠኛ ተቋማትን የማደራጀትና የማጠናከር ሥራዎችን ሊያከናውን እና ውጤታማነታቸውንም ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 3. ሚ/ር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ለዘርፉ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምርና ሥርፀት ሥራዎችን ማካሄድ አለበት፡፡ |
| | 4. ሚኒስትር መ/ቤቱ አዳዲስ ሥልጠናዎችን ለመስጠት የሚያስችሉ ካሪኩለም ቀረጻ በማከናወን መምህራንን ማብቃት አለበት፡፡ |
| | 5. ሚኒስትር መ/ቤቱ የኢንደስትሪ ንዑስ ዘርፎቹን ለመደገፍ የተቋቋሙትን ኢንስቲቲዩቶች አቅማቸውን በዘላቂነት የሚገነባበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል ፡፡ |
| | 6. ሚኒስትር መ/ቤቱ በየንዑስ ዘርፉ በተቋቋሙ ኢንሰቲቲዩቶች የኢንዱስትሪዎቹን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ሥልጠናዎችን በስፋት እንዲሰጡ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 7. ሚኒስትር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር የሰው ኃይልን በማብቃት ለኢንደስትሪው የሚያስፈልግ የሰው ኃይል የሚሟላበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 1.2 ሚኒስቴሩ የኤክስፖርት መር-የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን በመከተል፡ የኢንዱስትሪ የማምረት አቅምን፣ የምርት ጥራትን እንዲሁም የግብይት አቅምን በማጠናከር የኤክስፖርት ገቢን ከፍ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ፣ | 8. ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የወጪ ንግድን ለማሳደግ የኢንዱስትሪውን የማምረት አቅም ለማሳደግ በስፋትና በዘላቂነት ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 9. ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለውጭ ገበያ የተዘጋጁ የኢንዱስትሪ ምርቶች በወቅቱ ኤክስፖርት እንዲደረጉ የተቀናጀ የፋሲሊቴሽን ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡ |
| | 10. ሚኒስትር መ/ቤቱ ለኤክስፖርት ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚሰጠው የተለያዩ የማበረታቻ ድጋፍ ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ |
| | 11. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በግብይት ዙሪያ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት የአምራች ድርጅቶችን የኤክስፖርት ገበያ የመድረስ አቅማቸውን ለመገንባት ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡ |
| 2. በወጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ኢንደስትሪዎች የግብአት አቅርቦትና ምርት ትስስር ስራዎችን ማጠናከር፣ቁልፍ ሚና ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ለመስራት ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን እንዲሁም ተፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለሚመለከታቸው የሚሰራጭበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣<br>2.1 ለወጪንግድ በማምረት ላይ ለተሰማሩ ለኢንደስትሪዎች የግብአት አቅርቦትና ምርት ትስስር ስራዎችን ማጠናከርና ቁልፍ ሚና ካላቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር | 12. ሚኒስትር መ/ቤቱ ከኤክስፖርት ስራ ጋር በተያያዘ በጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ግብይት ስርዓት ላይ ለአምራች ላኪዎች የተለያዩ የግብአት አቅም ግንባታ ድጋፎች መስጠት አለበት፡፡ |
| | 13. የኢንዱስትሪ ሚኒሰትር የኢንዱስትሪ ምርቶችን በአለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ ወደ ተለያዩ የገበያ መዳረሻዎች መግባት የሚያስችል የግብይት ስትራቴጂ መንደፍና ስራ ላይ ማዋል አለበት፡፡ |
| | 14. ሚኒስትር መ/ቤቱ ወደ አገር ውስጥ ገቢ ምርቶችን የሚተኩ የአገር ውስጥ ምርቶች ለገበያ ተደራሽ እንዲሆኑ የግብይት ስትራቴጂ መንደፍና ስራ ላይ ማዋል አለበት፡፡ |
| | 15. ሚኒስትር መ/ቤቱ በሚያከናውኗቸው ድጋፎችና አገልግሎቶች ሂደት ከክልሎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር የሰመረ ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ማሳደግ አለበት፡፡ |
| | 16. ሚኒስትር መ/ቤቱ የኢንደስትሪ የወጪ ምርት ንግድን በሚመለከት በመንግስት የሚወጡ ፖሊሲዎችና የአፈፃፀም ህጎች ላይ ባለሃብቱን እና የዘርፍ ማህበራትን አሳታፊ የምክክር መድረክ መፍጠር አለበት፡፡ |

| | |
|---|---|
| በትብብርና በቅንጅት ለመስራት ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን ማጣራት፤ | 17.ኢንዱሰትሪ ሚኒሰቴር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የባለ ድርሻ አካላት ጋር በጋራ ተቀናጅቶ የማቀድ፣ የማስፈፀም የመከታተልና የመገምገም ስርአት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 18.ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጥራታቸውን የጠበቁ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለአለም ገበያ በስፋት እንዲቀርቡ በማድረግ  የተወዳዳሪነት አቅምን በስፋት ማሳደግ አለበት፡፡ |
| | 19.የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወደ ውጭ የሚላኩት የኢንዱስትሪ ምርቶች በህገወጥ መንገድ ከአገር እንዳይወጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የመከላከል ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 20.ሚኒስትር  መስሪያ ቤቱ ኢንዱስትሪዎች የግብርና ምርቶች ላይ እሴት ጨምረው ኤክስፖርት በማድረግ ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት እና ድጋፍ ማድረግ  አለበት፡፡ |
| | 21.የኢንዱስትሪ ሚኒስትር በየኢንዱስትሪ ዘርፎቹ የወጪ ንግድ ገቢ  በስትራተጂክ ዕቅዱ መጨረሻ ያስቀመጣቸውን ግቦች ማሳካት አለበት፡፡ |
| 2.2 በወጪ ምርት ማምረት ላይ ለተሰማሩ ኢዱስትሪዎች ተፈላጊ መረጃዎችን መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማቀነባበርና ለሚመለከታቸው የሚሰራጭበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ፣ | 22.የኢንዱስትሪ ሚኒሰትር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በማእከል የሚደራጁት ወቅታዊ፣ አለም አቀፍ እና የተሟሉ ዋና ዋና መረጃዎች በየጊዜው የማሰባሰብ፣ የማጠናቀር፣ የማደራጀትና የመተንተን ስራዎችን መስራት አለበት፡፡ |
| | 23.የኢንዱስትሪ ሚኒስትር በማእከል የተደራጁ መረጃዎችን የመረጃ ኔት ዎርክ በመዘርጋት ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ተጠቃሚዎች በተለያዩና በተሻሻሉ የስርጭት ዘዴዎች ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡ |

# አባሪ 2፡ ለዝርዝር ኦዲቱ በናሙና የተመረጡ

ለዝርዝር ኦዲቱ በናሙና የተመረጡ ኢንስቲትዩቶች ፣ኢንዱስትሪዎች እና የዘርፍ ማህበራት

በአካል መጠየቅ የቀረበላቸዉ ዝርዝር፤

**ከጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች**

1. አይካ አድስ ቴክስታይል
2. ባህርዳር ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማህበር
3. ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማህበር

**ከቆዳና ቆዳ ዉጤቶች ኢንዱስትሪዎች**

1. ኮምቦልቻ ታኔሪ
2. ኒው ዊንግ ጫማ ፋብሪካ
3. አንበሳ ጫማ ፋብሪካ

**ከብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች**

1. ኢንጀስኮ ኢትዮጵያ
2. ቤዛ ኢንዱስትሪ
3. ቴክኖ ሞባይል መገጣጠሚያ

**ከኬሚካልና ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪዎች ፤**

1. ደርባ መድሮክ ሲሚንቶ ፋብሪካ
2. ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ
3. ሸሙ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ከስጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች ፤**

1. አሸራፍ ኤክስፖርት ቄራ


**ከኢንስቲትዩቶች፤**

1. የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

**ከዘርፍ ማህበራት**

1. የኢትዮጵያ ቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ማህበር
2. የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ዘርፍ ማህበር

## አባሪ 3፡ የአሰራር ሥርዓት ትንተና (Process description)



# አባሪ 4፡ ድርጅታዊ መዋቅር

